# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ የአንደኛ ሩብ አመት የስራ አፈጻጸምን የያዘ መረጃ ዜና-መጽሄት

## መግቢያ

አገራችንን በ2022 ኢትዮጵያ "የአፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት" ለማድረግ ሀገራዊ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

የከተማ ልማት ስራም ባለ ብዙ ዘርፍ እንቅስቃሴዎችን ያካተተ ሲሆን ይህም የኢንዱስትሪ፣ የገበያ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ-ልማት አገልግሎቶችን በቅንጅት፣ በትስስርና በተመጋጋቢነት በውስጥም ሆነ ከአካባቢው ጋር በመፍጠር መምራት የሚጠይቅ ነው፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ስራችንም ከግብርና ቀጥሎ ሰፊ የሥራ እድል የሚፈጠርበትና የሀገራችን የኢንዱስትሪ መሰረትና ሁለንተናዊ ዕድገት የሚወስን ስትራቴጅክ ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም የልማት ስራዎች ምን አይነት አላማና ግብ ይዘው ከስራ ዘርፋቸው አቅጣጫ በተጨማሪ ወደ ጋራ ውጤትና የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ እንዲያመሩ በማስፈለጉ ይህንን አቅጣጫ የያዘ የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም ወደ ተግባር የሚያስገቡ የልማትና መልካም አስተዳደር ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ከዞኖችና ከከተማ አስተዳደሮች የተናበበ ዕቅድ እንዲኖረን በማድረግ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

በዚህም መሰረት የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ፣ የ5 አምስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድና የ2013 በጀት አመት እቅድ አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ2013 በጀት አመት በአንደኛ ሩብ አመት የተሰሩ ክንውኖችን የቢሮው ማናጅመንት ኮሚቴው ገምግመዋል፡፡ በግምገማው ላይም በአንደኛ ሩብ አመት ላይ ታቅዶ ያልተከናወኑ ክንውኖች በቀጣዩ ሩብ አመት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተተዋል፡፡ ከዚህም መነሻ የበጀት ዓመቱ የአንደኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ የስራ አፈጻጸምን በተመለከተ በየሩብ አመቱ እየተዘጋጀ በምትወጣው ዜና-መጽሄታችን ላይ እንደሚከተለው ለማቅረብ ሞክረናል፡፡

**የዝግጅት ምእራፍ የተከናወኑ ተግባራት**

ዕቅዱ በቢሮ ደረጃ የቅርብ ክትትል በሚደረግባቸው ቁልፍና ዋና ዋና ስራዎች ላይ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድና በ5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ የተቀመጡ ግቦች፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችንና የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን እንደ መነሻ ሁኔታ በመጠቀም የበጀት ዓመቱ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህ መልኩ የተዘጋጀውን ዕቅድ ፈጻሚን ከማዘጋጀት ረገድ በቢሮ ደረጃ ሁሉም ፈጻሚዎችና ዳይሬክቶሬቶች ከስራ ክፍሉ ሰራተኞች ጋር በዕቅዱ ዙሪያ እንዲወያዩ ከተደረገ በኃላ በቢሮ ማናጅመንት ከጸደቀ በኃላ ሁሉም የቢሮ አመራርና የተለያዩ ባለሙያዎች በተገኙበት ለ1 ቀን በቆየ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት የ2012 በጀት ዓመት እቅድ የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫ ዙሪያ የተቋሙ ሠራተኞች ጋር ዉይይት በማድረግ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

በዚህም የሴክተሩን የ2013 ዕቅድ በውጤት ተኮር ስርዓት መሠረት በማዘጋጀት ከዳይሬክቶሬቶች ጋር ለመፈራረምና ለፈጻሚዎች በማውረድና እንዲተገብሩት መግባባት ላይ ለመድረስ እየተሰራ ሲሆን ወደ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የማውረድና የመፈራረም ስራም በዚሁ መልኩ በመስራት ተቋማቱ ዕቅዱን በየደረጃው የማውረድ ስራ እንዲሠሩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ወደ ትግበራ ለመግባት ተችሏል፡፡

የ2013 በጀት ዓመት የ1ኛው ሩብ ዓመት የግቦች አፈጻጸምን ስንመለከት፡-

## የተገልጋዮችን ዕርካታ ከማሳደግ አንጻር ፡-

- የተገልጋዩን ዕርካታና አመኔታ ለማሳደግ ወደ ተቋሙ የሚመጡትን አቤቱታና ቅሬታዎችን መፍትሔ መስጠት ጋር ተያይዞ ወደ ተቋሙ ከሚመጡ አቤቱታዎች መካከል 60% ምላሽ በመስጠት ከፈርጅ ሁለት እስከ አምስት የሚገኙ ከተሞች በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት የነዋሪው ዕርካታ ደረጃ በመመዘን 60 በመቶ መድረሱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የ5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ እና የ2013 በጀት ዓመት የሴክቴር ዕቅድ በማዘጋጀት የመናበበ ስራ የተሰራ ሲሆን የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ ከ7 የታችኛው ተቋም ጋር መፈራረም ተችሏል፡፡
- የዘርፉን የፊዝካል ዕቅድ የአፈጻጸም 1 ጊዜ የዘርፉን የፊዝካል ዕቅድ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በማድረግ 1 ተቋማዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡

## የከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር አቅም ማሳደግን በተመለከተ፡-

- በከተሞች የገቢ አሰባሰብ የህግ ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ 1 የገቢ ማሳደጊያ እቅድ (REP) በማዘጋጀት 0.0171 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በክልሉ ያሉ ሁሉም ቁጠባ ቤቶች 86,767 ብር ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡
- በአሶሳ ከተማ ላይ የሃብት አስተዳደር ዕቅድ (AMP) በማዘጋጀት 95 በመቶ ተግባራዊ እንዲያደረግ ሲሆን በተጨማሪም የመዋዕለ ንዋይ እቅድ /CIP/ በማዘጋጀት 82% እንዲተገበር ተደርጓል፡፡

## የበጀት አጠቃቀምና አያያዝ ስርዓት ከማሻሻል አኳያ፡-

- በበጀት ዓመቱ ለቢሮው ከመንግስትና ከተለያዩ ምንጮች የሚመደበውን የመደበኛና የካፒታል በጀት በአግባቡ በመጠቀም ለታቀደለት ስራ የማዋል ስራ እየተሰራ ይገኛል።
- የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ለማስኬድ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚመደበውን በጀት ለታቀደለት ስራ ከማዋል አንፃር ለቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች 653,940.00 ብር ለመክፈል ተችሏል።

| የወጪ ዓይነት | የተስተካከለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ | ሽፋን በመቶኛ | ምር መራ |
|---|---|---|---|---|
| ደሞዝ | 9,753,054 | 2,078,250.45 | 21% | |
| ስራ ማኬጃ | 3,327,785 | 781,143.01 | 23% | |
| ድምር | 13,080,839 | 2,859,423..46 | 22% | |

## የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ማሳደግን ስንመለከት፡-

- በከተሞች በሊዝ የሚተላለፍ ቦታ በአገልግሎት አይነት ለይቶ ለማዘጋጀትና ለማስተላለፍ በከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 5.91 ሄክታር በምደባ ለማስተላለፍ ተችሏል።
- በክልሉ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች ቦታ በምደባ ከመስጠት አኳያ ለ57 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት መሬት በመስጠት በ57 የኢንቨስትመንት ቦታዎች ላይ በውላቸው መሰረት መሰራታቸውን ክትትል ለማድረግ ተችሏል። በተጨማሪ ለ2 (100%) በርበር እና ዶቢ ከተሞች የሊዝ ዋጋ ክለሳ እና የቦታ ደረጃ የሚያሳይ ካርታ ለማዘጋጀት ተችሏል።

## የከተማ ፕላን ዝግጅት እና ትግበራን ማሳደግን በተመለከተ፡-

- የፕላን አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር በተመለከተ በ2 ከተሞች ማለትም በኡዳ እና በአሶሳ የመሬት አጠቃቀም አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በዳዛ 119 ብሎክ፣ በሆሞሻ 50 ብሎክ፣ በባምባሲ 2 ብሎክ በድምሩ 179 ሄክታር ብሎክ ለመክፈት የተቻለ ሲሆን 30 ለሚሆኑ ተነሳሽዎች የቦታ ሽነሽና ተደርጓል።

## በከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንጻር፡-

- በከተማ ልማት ስራዎች የስራ ዕድል ፈጠራን ከማሳደግ በበጀት ዓመቱ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለ51 ሴቶች እና ለ201 ወጣቶች በድምር ለ252 ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ተችሏል።

- በከተሞች የሚገኙ የመስራት አቅም የሌላቸው እና ለማህበራዊ ችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍል የመሰረታዊና የማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ከማድረግ አኳያ 600 ዜጎች የቀጥታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ተችሏል።

## የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ስንመለከት፡-

- የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች፣ የስራ ተቋራጮች፣ የአማካሪ ድርጅቶች፣ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች እና የግብዓት አቅራቢዎች ከመመዝገብ አኳያ በዚህ ሩብ ዓመት 45 የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችን እና 37 የስራ ተቋራጮችን ለመመዝገብ ተችሏል፡፡
- ለ10 ባለሙያዎች እና ለ2 የስራ ተቋራጮች ኢንስፔክሽን ስራ ተከናውኗል።

## የተቀናጀ ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቀ የመሠረተ-ልማት አቅርቦትና ተደራሽነትን ከማስፋፋት አኳያ፡-

- በከተሞች ማህበራዊ ደህንነትን መሰረት ያደረገ፣ ደረጃውን የጠበቀ፣ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ፣ የተቀናጀ መሠረተ-ልማት አቅርቦት መርህን መሰረት ያደገ መሰረተ-ልማት አውታሮች ግንባታ እና ጥገና ከማድረግ አንፃር 0.5 ኪ.ሜ ኮብል ስቶን እና 1.43 ኪ.ሜ ጎርፍ ማስወገጃ /ዲች/ በአሶሳ ከተማ ለመገንባት ተችሏል።

## ተደራሽና ደረጃውን የጠበቀ የቤት አቅርቦትን በተመለከተ፡-

- በመኖሪያ ቤቶች በማህበር እና፣ በግለሰቦች የተለያዩ አይነት ያላቸው ቤቶችን መገንባት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በዚህ ሩብ ዓመት 148 የተለያዩ አይነት ያላቸው ቤቶች በአሶሳ ከተማ መገንባት ተችሏል፡፡

## የህንጻ ግንባታ አስተዳደር ስርዓት ማሻሻልን ስንመለከት፡-

- በሚገነቡ በ4 የመንግስት ህንፃዎች (ኩርሙክ /ዱሽታሎ/፣ አሶሳ /ጉንባ/፣ ከማሽ ከተማ አስተዳደር እና መተከል ዞን) ላይ ክትትልና ቁጥጥር ስራ ለመስራት ተችሏል፡፡
- በክልሉ የመንግስት ነባር ህንጻዎችንና አዲስ ፕሮጀክቶችን በመመዝገብ የግንባታ መረጃዎችን በተፈለገው ጊዜ፣ ዋጋ ግምት የማቅረብ ስራ ለማከናወን ታቅዶ የ61 ነባር የመንግስት ህንጻዎች መዝገባ ተከንውኗል።
- የጥገና አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ህንጻዎች እንዲጠገኑ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመወያየት ሃሳብ በማቅረብ የህንፃ ሀብቶችን የመንከባከብ፣ የመጠበቅና በጥንቃቄ የመጠቀም ልምድን የማዳበር ስራዎችን በመሪነት እንዲከናወኑ በሩብ ዓመቱ የጥገና

አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው 61 ነባር የመንግስት ህንፃዎች /211 ቤቶች/ የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡

- በክልሉ በጀት ለሚሰሩ ለ18 አዲስ ግንባታ ዲዛይንና የስራ መዘርዝር ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡
- የህንጻ አዋጁ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው ከተሞች ለሚገነቡ 24 ህንጻዎች የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና መረጃ ስራ አመራር ከማሻሻል አንጻር፡-

- የከተሞች ገቢ አሰባሰብ ስታቲክስ፣ የመሰረተ-ልማት መረጃ፣ የከተሞች የህዝብ ተሳትፎ ስታቲክስ፣ የከተሞች የሰው ሀይል ፕሮፋይል መረጃና የከተሞች የሶሾ ኢኮኖሚ ጥናት መረጃ 91 በመቶ ተደራጅቶ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

በማጠቃለያ በዘርፉ በ2013 በጀት ዓመት በ1ኛ ሩብ ዓመት የተጣሉ ግቦችን ለማስፈጸም በየእርከኑ በሚገኙ አመራሮችና ፈጻሚዎች ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በሩብ ዓመቱ በተሰሩ ስራዎች አንፃር የግቦች አፈፃፀም ስንመለከት በከፍተኛ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የግብ አፈጻጸሞች ስላሉ በቀጣይ ያልተከናወኑ ተግባራትን ለይቶና ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ ይጠበቃል፡፡ ሰለሆነም በሩብ ዓመቱ ግቦቻችንን ለማሳካት ከየተቀረጹ ተግባራት መካከል አብዛኞቹ ታቅዶ ያልተከናወኑና በበጀት ዓመቱ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ከተዘረዘሩ ተግባራት መካከል አብኛው በቀጣዮቹ ሩብ ዓመት የሚከናወኑ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላቶች ተግባራቶችን ወደ ራሳቸው ወስደው በተሻለ የስራ ተነሳሽነት ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራው ይገባል፡፡

**የኮቪድ 19 መረጃዎች**

- **የሁለት አዋቂ እርምጃ ያህል ርቀታችንን እንጠብቅ!!**
- **እጃችንን በየጊዜው ለ 20 ሰኮንድ እንታጠብ/ከአልኮል የተዘጋጁ ማጽጃ/ሳኒታይዘር/ በመጠቀም የእጅዎን ንጽህና ይጠብቁ!!**
- **በሚያስሉበትና በሚያስነጥሱበት ወቅት በሶፍት ወይም ክንዶዎን በማጠፍ አፍና አፍንጫዎን ይሸፍኑ!!**
- **ባልታጠበ እጃችን አፍ፣ አፍንጫችንና አይናችንን አንንካ!!**

ውድ አንባቢዎቻችን የእናንተ ገንቢ አስተያየት ለስራችን ወሳኝ በመሆኑ በዜና-መጽሄታችን ላይ ያላችሁን አስተያየት ቢታደርሱን በደስታ እንቀበላለን!!

አዘጋጅ ፦ የቢሮው ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ስልክ 0577751802

ኢሜይል bgrs udcb@.gmail.Com

ፌስቡክ BGRS- Urban Development and Constraction Bureau

ጥቅምት 2013 ዓ/ም